# በአፍ የሚወሰዱ ጸረ-ቫይረስ መድኀኒቶች ምንድን ናቸው?

## COVID-19 ያለበት ሰው እንዲሻለው የሚረዱ ኪኒኖች ናቸው።

ከባድ ለሆነ የ COVID-19 በሽታ ተጋላጭ ከሆኑ እና ባለፉት 5 ቀናት ውስጥ COVID-19 ተመርምረው ፖዘቲቭ ከሆኑ፣ በሐኪም የታዘዙ በአፍ የሚወሰዱ የፀረ-ቫይረስ ኪኒኖችን መውሰድ ይኖርብዎታል። ሁለት ሕክምናዎች ቀርበዋል፡- ፓክስሎቪድ (Paxlovid)™ (Pfizer) እና ሌጌቪርዮ (legevirio) (Merck)። ዕድሜዎን፣ የጤና ታሪክዎን እና ምልክቶቹ ለምን ያህል ጊዜ እንደታየብዎት መሰረት በማድረግ ከእነዚህ የ COVID-19 ሕክምናዎች ለአንዱ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

በአፍ የሚወሰድ የፀረ-ቫይረስ ህክምና SARS-CoV-2 ቫይረስ (COVID-19 ን የሚያመጣው ቫይረስ) በሰውነትዎ ውስጥ እንዳይባዛ በማድረግ፣ በሰውነትዎ ውስጥ ያለውን የቫይረሱን መጠን በመቀነስ ወይም በሽታ የመከላከል ስርዓትዎን በማገዝ ሰውነትዎ COVID-19 ን እንዲዋጋ ሊረዳ ይችላል። ሕክምና በማግኘት፣ ምልክቶቹ ያን ያህል አሳሳቢ ያልሆኑ እንዲሆኑ ማድረግ ይቻላል ደግሞም ሕመምዎ እየተባባሰ እንዳይሔድ እና ሆስፒታል የመተኛት እድሎንም ይቀንሰዋል።

---

### • በአፍ የሚወሰድ ፀረ-ቫይረስን እንዴት እወስዳለሁ?

በአፍ የሚወሰድ የፀረ-ቫይረስ ህክምና ማግኘት ማለት ኪኒን ይወስዳሉ ማለት ነው። በጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ እንደተመለከተው በአፍ የሚወሰድ የፀረ-ቫይረስ ሕክምናን መውሰድ አለብዎት። የሚወስዱትን የቀኑን የመድኋኒት መጠን አይዝለሉ ወይም ሳልወስድ ቀረሁ ብለው ተጨማሪ መጠን አይውሰዱ። ሁሉንም ህክምናዎች እስኪያጠናቅቁ ድረስ ወይም የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ እንዲያቆሙ እስኪነግርዎት ድረስ እንደ መመሪያው መውሰድ አለብዎት። በአፍ የሚወሰዱ ፀረ-ቫይረስ መድሃኒቶች ከምግብ ጋር ወይም ያለ ምግብ ሊወሰዱ ይችላሉ እንዲሁም ኪኒኖቹ ሳይሰበሩ እና ሳይፈጩ ሙሉ በሙሉ እንዲዋጡ ይመከራል።

### • እንደ ኩላሊት ወይም ጉበት ህመም አይነት ስር ሥር የሰደደ የጤና እክል ያለብኝ ቢሆንስ?

ማንኛውንም መድሃኒት ከመውሰድዎ በፊት፣ የጤና ታሪክዎን ከጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ጋር መወያየት አለብዎት። ይህም ሊኖርብዎት ስለሚችሉ የጤና ሁኔታዎች እና የታዘዙልዎት መድሃኒቶች፣ ያልታዘዙ መድሃኒቶች፣ ቫይታሚኖች እና ስለሚወስዷቸው ሰፕልመንቶች ለእነርሱ መናገርን ያካትታል።

ማንኛውም አይነት የኩላሊት ወይም የጉበት ህመሞች ያለባቸው ሰዎች በአፍ የሚወሰድ ጸረ ቫይረስ መድሃኒቶችን ከመውሰዳቸው በፊት ስለ ሁኔታቸው ለጤና እንክብካቤ አቅራቢያቸው መናገር አለባቸው። የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ በአፍ የሚወሰደው ጸረ ቫይራል ህክምና ለእርስዎ ልክ መሆኑን ወይም ተገቢ ዶዝ መሆኑን ሊወስንልዎት ይችላል። የተወሰኑ ህክምናዎች የተወሰኑ ህመሞች ላለባቸው ሰዎች ላይመከሩ ይችላሉ።

### • በአፍ ለሚወሰድ የጸረ ቫይረስ ህክምና ብቁ የማልሆን ቢሆንስ?

የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ በአፍ ለሚወሰድ የጸረ ቫይረስ ህክምና ብቁ እንዳልሆኑ ወይም ለእርስዎ ልክ እንዳልሆነ ሊወስን ይችላል። ለዚህ ብዙ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ። ሁሉንም የብቁነት መሰፈርቶች ላያሟሉ ይችላሉ፣ ወይም ለተወሰኑ ህክምናዎች ተስማሚ ያልሆነ የጤና ሁኔታ ሊኖርብዎት ይችላል። ለእርስዎ ምርጥ የሆነውን ህክምና ከጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ጋር ይወያዩ።

DOH 825-029 May 2022 Amharic

ይህን ሰነድ በሌላ ቅርጸት ለመጠየቅ፣ 1-800-525-0127 ላይ ይደውሉ። መስማት ለተሳናቸው ወይም መስማት ለሚቸገሩ ደንበኞች፣ እባክዎ በስልክ ቁጥር 711 (Washington Relay) ይደውሉ ወይም ወደ mailto:ecivil.rights@doh.wa.gov ኢሜይል ይላኩ።